# <u>ዓይን አፋር ግንባር? አጥር የለው ጆሮ!!</u>

እንዲያው አልፎ አልፎ ፍርስ ፍርስርስ አድርጎ የሚያስቀን ነገር ባንሰማ ኖሮ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከመቃብር የቀዘቀዘ፣ ሲያንስም ደባሪ፣ በሀቅ ግን አበሳጭና ተስፋ አስቆራጭ ሆኖ በጨረሰን ነበር፡፡ አልፎ አልፎ ግን የሚያስቅ የሚያንከተክት ፖለቲከኛ ብቅ ይልና ችግራችንን ረስተን እንድንስቅ ያደርገናል፡፡ የታደለች ሀገር፡፡

ትዝ ይላችኋል በረከት ስምዖን በ97ኡ ምርጫ አልተሸነፍንም ግን ነፋስ ነው ለተቃዋሚዎች ድምፅ የከመረላቸው ያለውን?ሳይነጋ ጀምሮ በየምርጫው ጣቢያ ተገትሮ ታግሶ ድምፁን የሰጠው ሚሊዮን ሕዝብ ተረሳና የተፈጥሮ ነፋስ ከኢሕአዴግ ሳጥን ወደ ተቃዋሚዎቹ ሳጥን የምርጫ ወረቀቶችን ሰርቆ እያናፈሰ ሲያስገባ ተነገረን፡፡ ሰውየው የተናገረው የቀልዱን ባለመሆኑ ሳቃችን ም በረከተ ፡፡ መለስ ዜናዊም የሶማሊያን ድንበር ተሻገርን እንጂ መቸ ወረርን ብሎ ሲገረምና እናምነውም ዘንድ ሲማጠነን መሳቃችን አልቀረም፡፡ በየነ ጴጥሮስ ለኢትዮጵያ ፕሬዚዳንትነት ተወዳድሮ ሲወድቅ ኢሕአዴግና ዴሞክራሲ ተጣልተዋል ሲል፣ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በእስር ቤት (አዎ በዚያ በጉደኛው ከርቸሌ) የ600 ገፅ መፅሀፍ ፃፍኩ ማለት ብቻ ሳይሆን የወያኔን ኢዴሞክራ ሲያዊነት መቸ እንዳወቀ ሲነግረን፣ አዜብ መስፍን (ማዳም መለስ) ለልጆቼ ትምህርት ቤት ወጪ ለመክፈል የምቸገር ምስኪን ነኝ ስትለን፣ በሳቅ ፈርስናል፡፡ ምን የማይሰማው ነገር አለ ጆሮ!

ቅቅቅቅቅቅ!
አይሰማ የለ ጆሮ
አይውጥ የለ ጉረሮ
ሙሉነሽ ታሰረች አስረኛ ቢሮ--- ይባል የነበረውን ብዙዎች ታስታውሱ ይሆን?

እኔ ምን ቸገረኝ ለሕዝቡ ጫጫታ
የወሩ ደሞዜ ከመጣ ልደታ --- ያሉትንስ የፓርላማ አባሎች?

ፖለቲካ የሞት ሽረት ጉዳይ መሆኑ ቀርቶ የጡረታ መዝናኛ፣ በባዶ መውገርገሪያና የእነ እወቁኝ ባዮች መናኸሪያ ከሆነ ጊዜ ጀምሮ ቀልዱ ፈልቷል፡፡ ከዓመታት በፊት በዋሺንግተን ከተማ የምት ወጣ ጋፋት የምትባል ጋዜጣ ቢጤ ነበረች፡፡ አሳታሚዋ ጋዜጠኛ ሴት ባይሆኑም የኢሠፓ ካርድ ያላቸው ነርስ ነበሩ፡፡ ከረር ያልኩ ፀረ ወያኔ ብሄረተኛ ነኝ ባይ የነበሩት እኚህ ሴትዮ ዛሬ ጎንደር ተንፈላሰውና ወያኔን ተሸክመው እየኖሩ ያሉ ቢሆኑም ከቀልዱ አንፃር ያፈረሱን ግን አከብራቸዋ ለሁ ያሏቸውን አሜሪካዊ (ጆን ስፔንሰርን) በራሳቸው ስልጣን ሊቀ መኳስ ብለው በግብዣና በይፋ ሲሾሙ ነበር፡፡ ለሳምንት ያህል ጉድ ብለን በሳቅ ሞትን፡፡ ኢሠፓዋ ነርስ ግራ ቀኙንም በወያኔነት ሲከሱ ከርመው፣ አልፎም እባክዎ ረጋ ይበሉ ያላቸውን ሁሉ በጅምላ ትግሬ-ወያኔ ብለው ሲያወግዙ ተደምጠው ዛሬ ያው የሚገኙበት ቦታና ሁኔታ መቸም ማስተዛዘቡ አልቀረም፡፡

ሊቀ መኳስ ጆን ነፍሳቸውን ይማርላቸውና ነርሷ በምን ስልጣን ሾሙኝ አላሉም፡፡ የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው ሆኖ ነው መሰል፡፡ እንድርያስ እሸቴ ሻዕቢያ ስልጣን ከያዘ በኋላ ኢትዮጵያው ያንን በስነ ስርዓት ይዞ በፍቅር ሸኘ ሲል ጃልሜዳ ከወደቁት የኤርትራ ተፈናቃዮች ጋር ሆነን ስቀናል፡፡ አንድ ተፈናቃይ ነኝ ያሉ ግለሰብ ለአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ አድማጮች መድረክ በላኩት ደብዳቤ " ዶክተር እንድርያስ የተማሩትን ሁሉ አምላክ ያጥፋብዎ " ብለው የረገሙትንም ስንስ ማ የምፀት ሳቅ ስቀናል፡፡አንድ ሰሞን በማን ይሁን ባላውቅም የሱቅ በደረቴ ድርጅቶች የተባሉ ፈልተው ነበር--የአንድ ሰው ድርጅቶች፡፡ አመራሩም አባሉም አንድ ሰው ይሆንና ስሙ ግን ሞቅ ያለው ድርጅት የሆነ ፡፡ሰራዊት በሜዳ ሳይኖራቸው ወያኔን በወረቀት የገደሉት " ጥቁር አንበሶ ች" ዓይነት፡፡ ላም አለኝ በሰማይ አድርገው ያስቀሩን፡፡ በእነሱም ስቀናል፡፡ ወያኔ ሊገድለኝ ይፈል ጋልና ጠባቂዎች ያጅቡኝ ያሉና በወረቀት መግለጫ የወያኔን ጦር ገፈርሳም ሳይቀር የረፈረፉ ኮለኔልም ለአንድ ወቅት አስቀውን ነበር፡፡ አቶ አሰፋ ጨቦስ ትዝ አይሉም? ልደቱስ ፀረ ወያኔ ነኝ ሲል? መቸስ
ማል ጎደኒ ሆነ ? (በቁቢ መፃፉን ገና አልተማርኩምና አቶ ሌንጮ ቸኩሎ ጎበናይስት እንዳይለኝና በደኖ አድርጉት ብሎ እንዳያዝብኝ!)

በበኩሌ ፕሮፌሰር መስፍን የሰብዓዊ መብት አስከባሪ ኮሚቴ መሰረቱ ሲባልም ከፕሮፌሰር ስቬንሰን ጋር ሆኜ ከት ብዬ ስቂያለሁ፡፡ የደርግ መርማሪ ኮሚቴ የነበሩና ለ60ዎቹ መረሸን መካሪ ናቸው ተብለው በመንግስቱ ራሱ የተከሰሱት ሰው የሚታወቁት በአምባገነንነት ሳለ ዴሞክራት ሆነው ሲጨበጭብላቸው መሳቅ ይነስ? ዛሬ ያው ኮሚክ አዛውንት መሆናቸው ከነፖለቲካ ክስረታ ቸው ተጋልጧል፡፡ ወይዘሪት ብርቱካን ጫማ ሲያስሙ ስቀናል፡፡ ሚሊዮን ዶላር አለኝ ብሎ የፖለቲካ አቡን ልሁን ሲል አንድ የዋሺንግተን ሰው ስቀናል፡፡ ዜሮ ዜሮ ብሎ ፀረ ወያኔ ነኝ ብሎ ፤ ኤርትራም ድረስም ሄዶ ኡኡ ያለው ወደል ዘፋኝ ሮጦ ለወያኔ ሲያድር በሳቅ ልንሞት ትንሽ ቀርቶን ነበር፡፡በባዕድ ሀገር በተለይ የፖለቲካው መድረክ በሳቅ ገዳይ ነው፡፡ ሰዉ ከሀገራችን ሕዝብ መከራና ስቃይ በተጨባጭ ሩቅ በመሆኑ፤ ተሰማኝ የሚለው ብሶትም ከሩቅ እንደሚታይ እሳት ነውና (አያቃጥል አይፋጅ በግምት ካልሆነ )፤ ይባስ ብሎ ወያኔ የሚነሰንሰውን ሱካር ላስ ላስ ለማድረግ እሽቅድምዱም ስላለ ቃልና ተግባር አልገናኝ ብለው በሳቅ ሊገድሉን መሞከራቸው አልቀረም፡፡ ታድለናል እንበል? በአሁኑ ጊዜ ልባችንን እያፈረሱት ካሉት ቀልዶች ውስጥ ደግሞ የአርበኝነት እውቅና ሰነድ ብሎ ግንቦት 7 ቡድን የጀመረው ነው፡፡ የእኛ ሀገር ሕዝብ ሞኙ የአርበኝነት መለያው ከባንዳነት መራቅና ለውድ ሀገር መቆም-መታገል- መሰዋት መስሎት ሲሰቃይ ተዓምር ላሳያችሁ ቆራጣ ሐሙስ ቀረችኝ ባዩ ይህ ቡድን በቅርቡ 2000 ዜጎች እያንዳንዳ ቸው 500 የአሜሪካ ዶላር ካወጡ ድርጅቱ አንድ ሚለዮን ዶላር ላስ ሊያደርግ ስለሚችል በልዋጩ የአርበኝነት መታወቂያ ሰነድ ለአዋጪዎቹ ይሰጣል ብሏል፡፡ ወያኔም ቀደም ሲል 500 ዶላር አምጡና ልዩ መታወቂያ ልለግሳችሁ ብሎ በባዕድ የሚኖሩትን ሲደልል ነበር፡፡ በ 500

ዶላር አርበኛ መባልና ማረጋገጫ ሰነድ ማግኘት አያስቅም? ጫካ ገብቶ ታግሎ፤ ትግል ብሎ ለፍቶ፤
መራራና ሰቃይን ተቀብሎ፤መሰዋዕትነትንም ችሎ ነው አርበኝነት እያሉ ያስቸገሩን ላይ ከት ብለን ልንስቅ ዕድል አግኝተናል። በእርግጥ 500 ዶላር 5 ሺ ብር ነውና ድህነት ባጠቃት ሀገራችን ብዙ ሰው አርበኛ ነህ የሚል ሰነድ አያገኝም። ዘንድሮ ግን ትግልና ድርጅት የሀብታሞች ነው ተብሏልና ይህ አስገራሚ አይደለም።

በ 500 ዶላር አርበኛ ተባሉ
ማን ሙቱ አላችሁ በዱር በገደሉ?
ቅቅቅቅቅቅ ብላችሁ በሉ ዛሬ ሳቁ።

በዚህ ስቀን ሳናበቃ ደግሞ በ 30 ዓመት ውስጥ ሁለቴ ድርጅቱን የከዳ ግለሰብ የቀድሞ ጓዶቹን ከፈጁ የቀይ ሽብር ወንጀለኞች መድረክ ብቅ አለና ኦነግ ዓይነ አፋር ግንባር ነው ብሎ አንፈራፈረን። የምትህት ግንባሮች አይተናል--ዛሬም አሉ። ትምክህተኛና ጠባብ ግንባሮችም ሞልተውናል። ዓይን አፋር ግንባር? ይህ የመጀመሪያ ከመሆኑ ሌላ በሳቅም እየገደለን ነው። ግንባር ዓይን አፋር ሆነ ሲባል ምን ማለት ነው? ፕሮግራሙን መርህ ግብሩን ይደብቃል? መሪዎቹ ቅልስልስ ይላሉ? ጠላት የለንም ይላሉ? ጠላታቸው ፊት ጎንበስ ለፈስፈስ ይላሉ? ምንድ ነው ይህ አስቂኝ ፍጡር? ለመሆኑ ኦነግ አይን አፋር ነው? አይኑን ጨፍኖ አንገቱን ደፍቶ ነው አሶሳ ጎጃም ሰፈር ያን ሁሉ ሕዝብ የጨረሰው? በደኖ ፍጅት ያካሄደው? ኦነግ ኢትዮጵያዊ አይደለንም፤ኦሮሚያ ቅኝ ግዛት ናት ትገንጠል ወዘተ ሲል መቸ አፈረ? ወይስ ኢትዮጵያዊ ነው ማለቱ ስላነቀው ነው ዓይን አፋር የተባለው? ወይስ ይህን ያለው ግለሰብ ነው አሳፋሪ ፍጡር? መንግስቱ ኃይለማርያም ሲመቸው ቀለስለስ፤አንገት ደፋ ማድረግና ዝንብም አልገደልኩ ማለት ይወድ ነበር። ዓይን አፋር እንበለው? ዓይን አፋር ሁለት መቶ ሀምሳ ሺ ሰው በሽብር ይበላል? ስለ ዓይን አፋር ግንባር አዲስ ግኝት ያስደመጠን ግለሰብ ምስጋና ይግባህ ዶክተር እንዳንለው በክህደቱና በዚህ ዓይነቱ ቅሌቱ እንጂ በሌላ ዶክተር ሲባል አልሰማንም። ግን ይህ ግኝቱ ዕፁብ ድንቅ ነው። የኦነግ መሪዎች ሰብሰብ ብለው አንገት ደፋ አደርገው ሲቅለሰለሱ መገመት ችለን ሳቅ ሞትን። የኦነግ መሪ የሆኑት ብዙዎቹ የደርግ ጊዜ ቀበልተኛና ከፍተኛ ሹመኞች ነበሩ። ሌንጮ ለታ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን ትምክህተኛ ሲል መች አፈረ? ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር ግንኙነታችን በአዳም ልጅነት ብቻ ነው ሲል መች አፈረ? መለስ ቪዛ ሰጥቶና አዋርዶ ከሀገር ውጡ ሲላቸው (ስንት ሺ የኦነግ አባል ታስሮ ባለበት!) ሌንጮና ዲማ ኖጎ በኤርትራው ኃይሌ መርቆሪዎስ አቅራቢነት መለስን ሲሰናበቱ (!) የነበረውን የመላቀስና የአንገት መድፋት ቲያትር ያስታውሰናል። ሌላ ፍንዳታ!!

በጉዳዩ ሳቅ በማብዛታችን የተናደደ ግለሰብ ስለ ዓይን አፋር ግንባር ከዚሁ ጉድ አቅራቢ ጋር ያደረገውን ቃለ መጠየቅ ልኮልናል። እነሆ፤

ጥያቄ-- አቶ ሲቪል መሀንዲስ በመጀመሪያ ለምን ትላንት ጓዶቼ ያሏቸው የነበሩትን ከፈጁና ትላንት ድርጅቴ የሚሉትንም ዛሬም ሊያጠፉ ከተነሱ ሰዎች ጋ ሄደው ቃለ መጠይቅ ሰጡ?
መልስ-- ይህን ዓይነቱ ዝግነት ነው ተቃውመን የተገነጠልነው:: ከሁሉም ጋር ለመወያየትና ለመስማማት ዝግጁ ነን:: ስየ አብረሃ፤ሌንጮ ለታ፤የቀይ ሽብር ወንጀለኛ የሚባለው ለእኛ ትርጉም የለውም:: ሰፊ ቦርቃቃ ነን:: ቼንጅ ዊ ካን
ጥያቄ--በሉ ይኼን በዚሁ ልተወውና ዋናው ጉዳይ ወደ ሆነው ልመለስ:: ኦነግ በኢትዮጵያዊነት ያምናል ግን ዓይን አፋር ስለሆነ ነው ይህን የማይለው ያሉት ብዙ ጥያቄ አስነስቷል:: ምን ይላሉ?
መልስ--ኢትዮጵያዊ ነን ብለው ያምናሉ ግን ማለቱን ያፍራሉ::
ጥያቄ--ለምን?
መልስ-- ዓይን አፋር ስለሆኑ ነዋ:: አቶ ዳውድ ኢብሳ ብዙ ጊዜ በኢትዮጵያውያን ስብሰባ ሲገኙ አይተሃል? ይሄ ማፈር አይደለም?
ጥያቄ-- በድረ ገፃቸው ለምን አይፅፉትም ታዲያ? የሀበሻን ቅኝ አገዛዝ እንታገለላን ከማለት ይልቅ?
መልስ--ዓይን አፋርነታቸው ነው እኮ የልባቸውን የሚያስደብቃቸው! እኛ ከድርጅቱ ስንገነጠል አምባገነኖችን እንታገል አልን እንጂ ወያኔ ጋ መሄድ እንፈልጋለን አልን? የማያፍር እኮ የልቡን ይናገራል::
ጥያቄ-- የኦነግን ልብ ለማወቅ እንዴት ቻሉ?
መልስ--ቅቅቅ የስዬን ልብ እንዴት አወቅን? ተለጣፊነት ይሉታል ሌሎች ሲያሾፉ:: እኛ ብዙ ምሁሮች ዶክተሮች አሉን:: እንደ ወያኔ ፕሮፌሰሮች ባይኖሩንም ምንም አንል:: ደህና ነን:: ዶክተር ዜሮዎች ቢሉንም:: ወደ ጥያቄዎች ለመመለስ የኦነግ መሪዎች ውስጥ ወዳጆች አሉን::
ጥያቄ-- ዓይነአፋር ድርጅትን በምን ማወቅ እንችላለን?
መልስ-- ለስላሳ ነው:: ሁሌም ሕዝብ ጠላት ከሚለው ጋር መደራደር ይፈልጋል:: ኦነግ በለንደን ተደራድሮ  ወደ ስልጣን መጥቶ ነበር እኮ:: ከዚያም በምስጢር ሁሌም ከኢሕአዴግ ተደራድሯል
ጥያቄ  ሌላስ?
መልስ-- የልቡን አያወጣም:: ይደብቃል::
ጥያቄ-- እነ ስዬ ታዲያ ኢትዮጵያዎ ሆነናል ሲሉ የልብ አይደለም ማለት ነው?
መልስ--አዎ
ጥያቄ-- ታዲያ ለምን ድጋፍ ሰጣችኋቸሁ?
መልስ--እንደ እኛ ዓይን አፋር ስለሆኑ::
ጥያቄ- በመሰረቱ ግን የአቅዋም ለውጥ የላቸውም ማለት ነው?
መልስ--ሊኖርም ላይኖርም ይችላል?
ጥያቄ-- ክፍት ነዋ?
መልስ--አይመስለኛል::

ጥያቄ-- አይመስለኛል?

መልስ-- ይመስላል፤ አይመስልም።

ጥያቄ-- እርሶ ደግመው ደጋግመው ድርጅት ሲከዱ ምን ይሰማዎታል?

መልስ--- ቅቅቅ ብተና አካሂጄ ሞት ለኢሕአፓ ካልኩ በኋላ መልሰው አመራር ያደረጉኝ ላይ እስቃለሁ። ቅቅቅቅ

ጥያቄ-- ዛሬ ታዲያ ስዬ ቪቫ፤ ሌንጮና ኦነግ ቪቫ ሲሉ በቀል ነው?

መልስ--ቅቅቅ አይመስለኛል!

ይህን ቃለ መጠይቅ መልሼ መላልሼ ባነብም የዓይነ አፋር ግንባር ቁልፉና ምስጢሩ በሚገባ ተረዳኝ ማለት አልቻልኩም። ኢትዮጵያዊ አይደለንም ለማለት የደፈሩ ኢትዮጵያዊ ነን ማለትን ለምን ያፍራሉ? እስቲ እናንተም ሳቁን ቆም አድርጉና ስለ ዓይነ አፋር ግንባር ግንዛቤያችሁን አካፍሉን። የአርበኝነት ሰነድ? ቅቅቅቅ ዓይነአፋር ግንባር? ዓይነ አፋር ነፍሰ ገዳይ? ቅቅቅ በሳቅ ብፈርስ ይቅርታ አድርጉልኝ።አፈረ ደፈረ ገዳይ ገዳይ፤ጠባብ ጠባብ፤ገንጣይ ገንጣይ፤ አንጃ አንጃ ባንዳ ባንዳ ነው።የማያስቅ ሀቅ!! በመጨረሻም ዓይን አፋሩ ታምራት ላይኔ ሲለቀቅ አሳሪዎቹን አመስግኖ አስቆናል። ደልሎ ላስ ብሎ በስዊስ ባንክ ያለውን 8 ሚሊዮን ሊበላ ይሆን?

ብንያም ዳዊት

ዘብሔረ ኢትዮጵያ